# ክርስቲያን ለመሆን ወስኛለሁ ከዚያስ?



## መግቢያ

ከጥንታዊት የግሪክ ከተሞች አንዷ በነበረች ከተማ የወኅኒ (እስር ቤት) ጠባቂ የነበረ አንድ ሰው፥ የሰው ልጅ ሁሉ በሕይወት ዘመኑ ሊጠይቅ የሚገባውን ታላቅ ጥያቄ ጠየቀ።

“እድን ዘንድ ምን ላድርግ?”

በቁጥጥሩ ሥር የነበሩት ሁለቱ እስረኞች (ጳውሎስና ሲላስ) ለዚህ ሰው ጥያቄ ትክክለኛው መልስ ነበራቸው።

“እነርሱም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰዎችህም ትድናላችሁ አሉት።” (የሐዋርያት ሥራ 16፥31)

የወኅኒ ጠባቂውም እንደተነገረው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አመነ ... ዳነም።

ከዚያም በኋላ ወደ ጳውሎስና ሲላስ ተመልሶ “ከዚያስ?” ብሎ ሳይጠይቅ እንዳልቀረ ይገመታል። ይህንን ለማረጋገጥ ከዳነ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ያደረጋቸውን ጠቃሚ ነገሮች በመመልከት መገመት ይቻላል።

ምናልባትም እርሰዎ በቅርቡ በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት አምነው፥ በመዳንዎ ተደስተው፥ ከዚያስ ምን ላድርግ የሚል ጥያቄ ለማቅረብ ተዘጋጅተው ይሆናል። ከሆነ፥ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን አስር ርምጃዎች ለመውሰድ ቢነሳሱ እጅግ የሚያረካና የሚያድግ የክርስትና ሕይወት ሊኖርዎ እንደሚችል እናምናለን።


© 2007 የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተክርስቲያን HOUSTON, TEXAS



ሳዖል በመባል የሚታወቅ አንድ ሰው እግዚአብሔርን እንዴት ሊያስደስት እንደሚችል በማሰብ ይጨነቅ ነበር። የእርሱም ታሪክ እንዲሁ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል።

በክርስቶስ ኢየሱስ አማኝ ከመሆኑ አስቀድሞ፥ እግዚአብሔርን ሊያስደስት የሚችልበትን ሐይማኖታዊ መንገዶች ሁሉ ይመረምር ነበር። በእርሱ እምነት፥ ራሱን ይገምት የነበረው በጽድቅ እንደሚኖር አድርጎ ነበር። በእርግጥም ብዙ መልካም ነገሮችን አድርጎ ነበር።

አንድ ቀን ግን ከኢየሩሳሌም ወደ ሶርያ ዋና ከተማ ደማስቆ በመጓዝ ላይ ሳለ፥ ሳዖል የኢየሱስ ክርስቶስን ድምጽ ሰማ። ወዲያውኑ ቀድሞ እንደሚያሰበው ሳይሆን ኃጢአተኛ እንደሆነ ተረዳ። በእግዚአብሔርም ኃይልና ጸጋ በአስገራሚ ሁኔታ ዳነ። ስለ ሕይወት የነበረው አመለካከት በጥቅሉ ተቀየረ። በምንም ዓይነት ቀድሞ እንደ ነበረው ሊሆን አልቻለም። ከዚህ አስደናቂ ለውጥም የተነሳ በኋለኛው ሕይወቱ ሃዋርያው ጳውሎስ ተብሎ ለመጠራት በቃ።

# 1

# ለመዳንዎ ርግጠኛ ይሁኑ

ጳውሎስም በኢየሱስ ካመነ በኋላ፥ እንዴት አንድ ሰው ሊድን እንደሚችል አስተማረ። ቅዱሳት መጽሕፍትን በማጥናትና የራሱን የሕይወት ልምድ በሚገባ በመመርመር፥ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ ጻድቅ ሊሆን የሚችለው በእምነት ብቻ መሆኑንና ቀድሞ ያስብ እንደነበረው ሕግን በመጠበቅ እንዳልሆነ አመነ ... አስተማረም።(ሮሜ 3፥28)

ለመዳን የሚያስፈልገው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ ነው። በእርሱ ብቻ ይመኑ፥ ማድረግ ያለብዎ ያንን ብቻ ነው።

ያንድ ቤተ ክርስቲያን አባል በመሆንዎ ጽድቅን ሊያገኙ አይችሉም። የምንም ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ዓባል መሆን አያድንም።

የሠሩት መልካም ነገር ተመዝኖ ከሠሩት መጥፎ ነገር ከበለጠ የሚጸድቁ ከመሰለዎ ተሳስተዋል። ምክንያቱም መቼም ቢሆን መልካም ሥራዎ መጥፎ ኃጢአትዎን ሊበልጥ አይችልም።

የሚጸድቁት በአዳኙ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመኑ ብቻ ነው። ኢየሱስ በመስቀል በተሰቀለበት ጊዜ፥ አንድ ሌባ ከጎኑ በሌላ መስቀል ተሰቅሎ ነበር። ይህ ሌባ ወደ ኢየሱስ ፊቱን አዙሮ፥ “ጌታ ሆይ በመንግሥትህ አስበኝ።” ሲል ጠየቀው። (ሉቃስ 23፥42)

ማንም ሰው ያለ ትክክለኛው እምነት ይህ ሰው የተናገረውን መናገር አይችልም። አመነ። ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት። “ዛሬ በገነት ከኔ ጋር ትሆናለህ። “

ያ ሌባ ሊጠመቅ የሚችልበት ዕድልም አልነበረውም። የቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን የሚያስችልም ዕድል አልነበረውም ምክንያቱም ጥያቄውን ሲያቀርብ በሞት አፋፍ ላይ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስን ለማመን ግን በቂ ጊዜ ነበረው።

ልክ እንደርሱ እርስዎም ለመዳን ማድረግ ያለብዎ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ ነው።

እምነቱ ታድያ የራስዎ መሆን አለበት (ሌላ ሰው ለእርስዎ ሊያምንልዎ አይችልም) የቤተሰብዎ አባል አማኝ ቢሆን እርስዎ ለራስዎ ካለመኑ አማኝ አይደሉም። መዳንዎ በሌላ በማንም ስው በኩል ሊመጣ አይችልም። (በቀሳውስት፣ ፓስተሮች ወይም በራባዮች አማካኝነት መዳንዎ ሊመጣ አይችልም የሚድኑት ርስዎ በሚወስዱት ርምጃ ብቻ ነው።) አንድ ጊዜ ይህን ርምጃ ከወሰዱ በአስተማማኙ በጌታ እጅ ውስጥ ይገኛሉ።

የኢየሱስ ቃል ኪዳን ለርስዎ እነሆ “በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ፥ እኔም አውቃቸዋለሁ፥ እነርሱም ይከተሉኛል፥ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ። ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ ከሁሉም ይበልጣል። ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም።”(ዮሐንስ 10፥ 27-29)

እንግዲህ ለማዳንዎ በክርስቶስ ኢየሱስ መታመንዎን ይጠይቁ።

በዚህ እርግጠኛ ከሆኑ፥ በልዑል እግዚአብሔር እጅ ውስጥ እንዳሉ ይመኑ። ከዚህ የተሻለ ምንም ስፍራ የለም። ክርስቲያንም ለመሆን የመጀመሪያውን እርምጃ ወስደዋል ማለት ነው።

ከዳኑ በኋላ ይህንን መልካም ዜና ለሌላ ሰው መንገር እጅግ አስፈላጊ ነው።  ክርስቶስ ወደ ሕይወትዎ እንደገባ ይናገሩ።  ይህ ማለት የኢየሱስ ምስክር ሆኑ ማለት ነው።  ኢየሱስ ሁላችንም የእርሱ ምስክሮች እንድንሆን ይፈልጋል።

መዳንዎን በሚመለከት ትክክለኛ የሆኑትን መልሶች መስጠት አይጠብቅብዎትም። በሕይወትዎ የሆነውን ሁሉ ላይረዱ ይችላሉ። ነገር ግን ለሰዎች የመዳንዎን ጉዳይ

# 2

# መዳንዎን ለሌሎች ሰዎች ይንገሩ

በሚናገሩበት ጊዜ ስለጉዳዩ ያለዎትን አስተሳሰብ እያጠራው ይሄድና በቅርብዎ ያሉትን ሰዎች ከጌታ ጋር ፊት ለፊት እንዲገናኙ ይረዳቸዋል።

በሕይወትዎ ስለሆነው ነገር መናገርዎ፥ በሚያውቁአቸው ዕውነቶችና ባሉዎ ጥያቄዎች መካከል ግልጽ ልዩነት መፍጠር እንዲችሉ ስለሚረዳዎ፥ በራስዎ  አዕምሮ የሆነውን ነገር በዕውቀት ያጸናልዎታል።

ለሰዎች ሲናገሩ በሕይወትዎ ከሆነው ነገር የተነሳ በደስታ ተውጠው ሊሆን ይችላል። ምንም እንኳን የሚነግሩአቸው ሰዎች እንደርስዎ እንዲያምኑ ጉጉት ቢኖርዎትም፥ ታጋሽ መሆን ይጠብቅብዎታል።  በጭራሽ አይከራከሩ።  በክርክር ጌታን የተቀበሉ ሰዎች የሉም። እርሰዎን ወደ እርሱ ያቀረበ ያ ንጹሕ ፍቅር ግን እነርሱንም ወደ እርሱ ሊያቀርባቸው ይችላል።




© 2007 የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተክርስቲያን HOUSTON, TEXAS

በኢየሱስ ክርስቶስ ባለዎ እምነት ማደግ ይኖርብዎታል። ለዚህ ታድያ በየቀኑ ቢቻል በተወሰነ ሰዓት እርስዎና ጌታ ብቻ አብራችሁ የምትሆኑበትን ጊዜ መለየት እጅግ አስፈላጊ ነው። በጸጥታ ከጌታና ከቃሉ ጋር መሆን በጣም ጠቃሚ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለኛ የልቡን የተናገረበት መጽሐፍ ነው። እንድናውቃቸውና በሥራ ላይ እንድናውላቸው አያሌ መመሪያዎችን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሰጥቶናል። እግዚአብሔር የሰጠን ልጁን ብቻ አይደለም። ልጁን ከመስጠቱ በተጨማሪ፥ እንድንመራበት ሕያው ቃሉንም ሰጥቶናል።

አንዳንዶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለመረዳት ትንሽ ከበድ ሊሉ ይችላሉ። አንዳንዶቹ እንደሌሎቹ ለማንበብ የሚመቹ አይደሉም። ቢሆንም ግን በሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እግዚአብሔር ለኛ ሊናገረን ያለው ነገር ስላለ ሁሉንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በጠቀሜታው እኩል ያደርገዋል።

# 3

# የጸጥታ ጊዜ ይኑርዎ

በየቀኑ በተወሰነ ሰዓት ያድርጉት እንጂ፥ ይህ የጸጥታ ጊዜ የግድ ጠዋት ወይም የግድ ማታ መሆን የለበትም። በጸጥታ ጊዜ ሊያደርጓቸው የሚገባ ስድሰት ነገሮች፤

በጸሎት ይጀምሩ። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለሚኖርዎ ጊዜ እንዲያዘጋጅዎ ይጠይቁት። በሕይወትዎ ጌታን ደስ የማያሰኝ ነገር እንዳደረጉ ካስታወሱ ለዚያ ይቅርታ ይናዘዙ። ይቅር እንዲልዎ በማድረግ በርሱና በእርስዎ መካከል ያለው ግንኙነት ምንም እንቅፋት እንዳይኖረው ያድርጉ።

የተወሰነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያንብቡ - አንድ ወይም ሁለት ምዕራፍ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በቅጡ የተዋወቁ ካልሆኑ ከአዲስ ኪዳን ቢጀምሩ መልካም ይሆናል። ብዙዎች የዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን ለመጀመር ጥሩ ስፍራ ነው ብለው ያምናሉ። ምናልባት በተጨማሪም ከመዝሙረ ዳዊት አንድ ሁለት ምዕራፍ ማንበብ ደስ ሊያሰኝዎ ይችላል።

ባነበቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሃሳብ ላይ ለጥቂት ጊዜ ያሰላስሉ። ስላነበቡት በማሰብ ያነበቡት እንዴት እንደገባዎ ራስዎን ይጠይቁ። እግዚአብሔር ምን እንዲያደርጉ ይፈልጋል? ምንም እንኳን ያነበቡትን ሁሉ ሊረዱ ባይችሉም የገባዎትን ያህል ሊታዘዙ እንደሚችሉ ያስታውሱ።

ያነበቡትን ክፍል በሚመለከት ያሉዎትን ጥያቄዎች ይጻፉ። ካነበቡት ውስጥ የገባዎትን ጉዳይና ያለዎትን ጥያቄ መጻፍ ጥሩ ነው። ከጸጥታ ጊዜዎ በኋላ በሚኖርዎ ጊዜ ለጥያቄዎ መልስ ሊሰጥዎ ከሚችል ሰው ወይም ከሌላ ምንጭ (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ የሊቃውንት አስተያየቶች መጻሕፍትና የመሳሰሉት።) መልሱን ለማግኘት ይሞክሩ። ቀደም ሲል ያነበቡትን ክፍል እንደገና ያንብቡ። ለሁለተኛ ጊዜ አንድን ክፍል ማንበብ ቀደም ሲል ሲያነቡ ያልተረዱአቸውን ነገሮች ወይም ልብ ያላሏቸውን ነገሮች በተሻለ መንገድ እንዲያስተውሏቸው ይረዳዎታል። ይህ በራስዎ ለመማር የሚችሉበት አንዱ መንገድ ነው። በሚያነቡበት ጊዜ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ሊያስተምርዎ አብሮዎ ይኖራል።

በመጨረሻ እንደገና ይጸልዩ። እግዚአብሔር አብ ልጁን በእርስዎ ምትክ እንዲሞት ስለጠዎ ያመስግኑት። ቃሉንም በመስጠት ራሱን ሊገልጥልዎ ስለወደደ ያመስግኑት፥ ምክንያቱም ያለዚያ መጽሐፍ በሕይወታችን ላለው ትልቅ ጥያቄ መልስ የምናገኝበት ምንጭ አይኖረንም ነበር።

ልብ ይበሉ፤ ብዙ አዲስ ክርስቲያኖች የጸጥታን ጊዜ በከፍተኛ ስሜት ይጀምራሉ። ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሥራ ብዛት ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን የጸጥታ ጊዜ ችላ ሲሉ ይታያሉ።

ለዚህ ቁልፉ መጽናት መቻል ላይ ነው። ከእግዚአብሔር ቃል በጥቂቱ የቀመሰ ሰው ብዙም የዚህ ሕያው ቃል ጣዕም አይታወቀውም። በየዕለቱ ለስጋዊ አካላችን ምግብ እንደሚያስፈልገንና እንደምንመገብ ሁሉ፥ እንዲሁ ከእግዚአብሔር ቃል በየዕለቱ መመገብ የዚያኑ ያህል አስፈላጊ ነው።

አንድ ጊዜ እባክዎን አያቋርጡ።

ከእግዚአብሔር ጋር በቅጡ መተዋወቅ ማለት ከእርሱ ጋር እንደ መልካም ወዳጅ መነጋገር ማለት ነው።  ጸሎት በቀላል አነጋገር ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ማለት ነው።

እግዚአብሔር ግልጽ የሆነና ታማኝነት የተሞላበት ውይይት ከልጆቹ ጋር በማንኛውም ሰዓት ቀንም ሆነ ሌሊት ማድረግ ይወዳል።

ይልቁንም የእግዚአብሔርን ቃል በምናነብበትና ቃሉን በምናሰላስልበት ጊዜ ጸሎት በጣም ጠቃሚ ሚና አለው።

# 4

# በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገሩ

መዝሙር 55፥17 “በማታና በጠዋት በቀትርም እናገራለሁ፥ እጮኽማለሁ ቃሌንም ይሰማኛል።” ይላል። ይህ ትክክለኛውን የመጸለያ ጊዜ ለማሳየት አይደለም። እግዚአብሔር በማንኛውም ሰዓት ከኛ መስማት ይፈልጋል።  ያም ቢሆን ግን የተወሰነ ሰዓት ለጸሎት ለይቶ መጸለይ ለመጀመሪያ ምንም አይልም።  እግዚአብሔርን እንደምን ወደው፣ እንደምናመሰግነውና ስህተታችንንም እየተናዘዝን በማንኛውም ጊዜ ይቅርታ ልንጠይቀው እንዲሁም ይቅርታውንም ልንቀበል እንችላለን።

ጸሎት የግድ ባማረ ቅንብር መቅረብ የለበትም።  ከልቡ ከሚወደን ወዳጃችን ጋር የምንነጋገር መሆናችንን መርሳት የለብንም።  ከማንም በላይ - ከራሳችንም በላይ ያውቀናል። ከዚህም የተነሳ ታማኝነት የተሞላበትን ዕውነት የሆነውን ሃሳባችንን እንድናካፍለው ይፈልጋል።

ሌላው ስለጸሎት ደስ የሚለው ነገር በምንጸልይበት ጊዜ ሁሉ ብቻችንን አይደለንም። ጌታ ኢየሱስና ጌታ መንፈስ ቀዱስ ከእኛ ጋር አብረው ሊጸልዩልን ቃል ገብተውልናል። የሮሜ መልዕክት ምዕራፍ ቁጥር 26 የምንጸልየውን በማናውቅበት ጊዜ እንኳን መንፈስ ቅዱስ እንደሚጸልይልን ይነግረናል።

በተሸነፍን ጊዜ እንኳን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይልልን ዘንድ ጌታ ኢየሱስ ስለኛ ከመሰዋቱ የተነሳ ይረዳናል።(1ኛ ዮሐንስ 2፥1)

ማንኛውንም ጉዳይ ለእግዚአብሔር በጸሎት ማምጣት መቻላችን ብቻ ሳይሆን መስማታችንም እርግጠኛ ነው። ጸሎት እንዲደረጉልን ወይም እንዲለወጡልን የምንሻቸውን ነገሮች ዝርዝር ይዘን በምንቀርብበት ጊዜ ብቻ አይደለም።  ይልቁንም በደንብ ከሚያውቀንና በደንብ ከምናምነው ወዳጃችን ጋር የምንነጋገርበት ጊዜ ነው።  አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ደስ በማይለን ሁኔታ ውስጥ በመተው ካለንበት የእምነት ደረጃ እንድናድግ ይተወናል።  በማንኛውም ሁኔታ ጸሎታችንን ይሰማል ይመልስማል።  ሁኔታው ለጊዜው ደስ የማያሰኘንም ቢሆን፥ የሚያደርገው ሁሉ ልጁን ክርስቶስ ኢየሱስን በመምሰል እንድናድግ በመሆኑ ለዚህ ግብ የሚጠቅመንን ሁሉ ያደርጋል።

ጸሎታችን እንዲሆኑልን ከምንጠይቃቸው ጉዳዮች በላይ ነው። በጸሎታችን የምናቀርበው ልመና ብቻ አይደለም።  ያም ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱት 667 ጸሎቶች 454 መልሶች ተመዝግበው ይገኛሉ።  ምንኛ የሚያበረታታ ነው።  መልስ ያገኙት ጸሎቶች እግዚአብሔር እኛን ልጆቹን ምን ያህል እንደሚያዳምጠንና ጸሎታችንን ለመስማትና ለመመለስም ምን ያህል ፈቃደኛ እንደሆነ ያሳያሉ።


© 2007 የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተክርስቲያን HOUSTON, TEXAS



ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ አዲስ ጓደኞች ሊያስፈልጉዎ ይችላል፡፡ እነዚህ አዲሶቹ ጓደኞችዎ እንደርስዎ ለጌታ ፍቅር ያላቸው መሆን ስለሚኖርባቸው በሕይወትዎ ሊገጥሙዎት በሚችሉ ደስ የሚያሰኙም ሆኑ ቅር የሚያሰኙ ጉዳዮች በጸሎት በመተጋገዝ የክርስትናውን ጉዞ አብራችሁ ለማዝግም ትረዳዳላችሁ፡፡

እንደዚህ ያለ ጓደኛ መልካም ነገር በሆነልዎ ጊዜ አብሮ በደስታ ይዘምራል፡፡ ሕይወትዎ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥም ሲያልፍ በጸጥታ አብሮዎ በመሆን ሕመምዎን ይካፈላል፡፡

# 5

# ክርስቲያን የሆኑ ጓደኞችን ያብጁ

ይህ ማለት ግን የቀድሞ ወዳጆችዎን ርግፍ አድርገው ይተዉአቸው ማለት አይደለም፡፡ እንደቀድሞው ሊወዷቸውና የእግዚአብሔርንም ፍቅር ሊያካፍሏቸው ይገባል፡፡ አንዳንዶቹ በሕይወትዎ የተካሄደው ለውጥ ግራ ሊያጋባቸውና የማይቀበሉት ደረጃ ላይ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ያም ቢሆን ይቀበሏቸው ይውደዷቸው፡፡

አዲሶቹ ክርስቲያን ወዳጆችዎ በክርስትና ሕይወትዎ ጸንተው እንዲቆዩና ሕይወትዎን እግዚአብሔር እንደሚያየው ማየት እንዲችሉ ያግዙዎታል፡፡ በክርስትና ሕይወትዎ ሊፀኑ የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻቹልዎታል፡፡

አዲሱ ሕይወትዎ ከቀድሞው የተለየ ከመሆኑ የተነሳ ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ሰዎች የሚኖርዎ ፍቅር በሕየወትዎ ትልቁን ስፍራ የሚይዙ ይሆናሉ፡፡

ክርስቲያኖቹ ጓደኞችዎ ያበረታቱዎታል፡፡ ደስታዎ እንዲበዛ ሃዘንዎ ደግሞ እንዲከፈል ከጎንዎ ይገኛሉ፡፡ ካከማቹት መንፈሳዊ ጥበብ ያካፍሉዎታል፡፡ ጠቢብ ከመሆን ቀጥሎ ያለው ጥሩ ነገር ጥበበኛ በሆኑ ጓደኞች አካባቢ መሆን ነው፡፡ ማወቅ የሚሹትን ነገሮች በቀላሉ ጠይቀው መረዳት የሚችሉበት ዕድል ይከፈትልዎታል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትዎ ያግዙዎታል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከርስዎ ጋር በመሄድ የእንግድነት ስሜት ከውስጥዎ በቶሎ እንዲወገድ ይረዱዎታል፡፡

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመኑ ወደያውኑ መጽሐፍ ቅዱስ የምታስተምር ቤተ ክርስቲያን አባል ይሁኑ።  አይዘግዩ።  ጌዜዎን፣ ዕውቀትዎን፣ ሙያዎንና ገንዘብዎን ወይም ሌላ ነገር ያላበረኩትበትን ቤተ ክርስቲያን መሰልቸት ይቻል ይሆናል።  ነገር ግን ባለዎ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዓላማ የተባበሩ ከሆኑ ከኅብረቱና ከምእመናኑ ጋር የጠበቀ መተሳሰር ስለሚፈጥርልዎ በዚህ የተጉ ይሁኑ።

ይህ መልካም ክርስቲያን ጓደኞች ያፈራልዎታል ከዚያም በላይ ደግሞ በክርስትና ሕይወትዎ በእመርታ ለማደግ አመቺ ሁኔታን ይፈጥርልዎታል።  የጥሩ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ፣ እርሱንና ቃሉን እንዲያከብሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርልዎታል።

# 6

# የጥሩ ቤተ ክርስቲያን አባል ይሁኑ

ቤተ ክርስቲያን ለመሰብሰብና ለመበተን መንታ ግብ ይዛ ትገኛለች።  በቤተ ክርስቲያን አብረን በምንገኝበት ጊዜ እንባረካለን።  ለመባረክ ብቻ ስንል ግን አይደለም ቤተ ክርስቲያን የምንሄደው።  የምንሄደው፥ እግዚአብሔርን እርሱን በጋራ ማምለካችን ደስ ስለሚያሰኘው ነው።  እግዚአብሔርንና ልጆቹንም በመሻት እንሄዳለን።

በቤተ ክርስቲያን በምንሆንበት ጊዜ መንፈሳዊ ባትሪአችን ጎልብቶ ስለምንወጣ ብርሃናችን በሰው ፊት የበራ እንዲሆን ይረዳናል።

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ማለት ዕውነተኛ አማኞች ናቸው።  (ማቴዎስ 16፥18) ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው።  (ቆላስይስ 1፥18)  ቤተ ክርስቲያን አካሉ ነች።  (ኤፌሶን 1፥22-23)  ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ እዚያ የምናገኛቸው ሰዎች እንደኛ ይቅርታን የተቀበሉና ገና ክርስቶስን ወደ መምሰል በመሰራት ላይ ያሉ ናቸው እንጂ ፍጹማን አለመሆናቸውን ማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚታይበትና ስልጣን ያለው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ የታመነበት፤ አባሎቹ በኃጢአታቸው ለሚጠፉ ሰዎች ግድ የሚሰኙበትና ጥልቅ በሆነ አክብሮት እግዚአብሔርን የሚያመልኩ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው መሄድ የሌለብዎ ከሆነ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥም ከፍ ሲል የማይሰሙ ከሆነ፥ በኃጢአታቸው ለሚጠፉ ሰዎች ጉዳይ አሳሳቢነት የማይነገር ከሆነ ከዚያ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ይራቁ።




© 2007  የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተክርስቲያን  HOUSTON, TEXAS



አንዳንዶች ለመዳን መጠመቅ አለብን ብለው ያስተምራሉ። ሌላው አመለካከት ግን ለመዳን ሳይሆን ለመታዘዝ እንጠመቃለን የሚለው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው፥ ለመዳን የሚያስፈልገን እምነት ብቻ እንደሆነ ከጥምቀት ጋር ሳይያያዝ እንመለከታለን። (ዮሐንስ 5፥24፣ የሐዋርያት ሥራ 16፥31፣ ሮሜ 10፥9-14)

የውኃ ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር ለመጣመር ያለንን ፍላጎት ያሳያል። (ሮሜ 6፥1-4) ለሚመለከቱን ሰዎች በዳንን ጊዜ በክርስቶስ አካል ውስጥ መግባታችንን ለማሳየት ከውኃ ጥምቀት ሌላ የተለየ መንገድ የለንም። ስንጠመቅ ክርስቶስ እንደሞተ በሞቱ መተባበራችንን፥ እንደተቀበረ መቀበራችንን፥ በትንሳኤም እንደተነሳ ተነስተን በአዲስ ሕይወት እርምጃ መጀመራችንን ማሳየታችን ነው።

# 7

# ይጠመቁ

የውኃ ጥምቀት ክርስቶስን ለመከተል ያለንን ፈቀደኛነትም ያሳያል። (ሮሜ 6፥4) ከድሮው ሕይወታችን ጋርና የድሮው ሕይወት ውጤት ከነበረው የኃጢአት ኑሮ ጋር ያለንን ግንኙነት በፈቃዳችን የመቁረጣችንም ምልክት ነው። ምንም እንኳን ከጥምቀት በኋላ ሙሉ ለሙሉ ከኃጢአት ነጻ መሆን ባንችልም፥ መጠመቃችን ወደ ሌላ አቅጣጫ መንገድ መጀመራችንንና በአዲሱ ጎዳና ለመሄድ የመጀመሪያውን ርምጃ መውሰዳችንን ለዓለም የምናሳይበት መንገድ ነው።

ጌታን በጥምቀቱ መከተል ማለት እርሱ ያደረገውን ማድረግ ማለት ነው። (ማቴዎስ 3፥16-17) ጌታን በጥምቀቱ መምሰል ማለት ለጌታ መቀየራችንን ማሳወቃችን ነው። (1ኛ ቆሮንቶስ 6፥19-20)

ጌታን በጥምቀት መከተል ማለት ከመዳናችን በፊት የነበረውን ሕይወት መተው ማለት ነው። (2ኛ ቆሮንቶስ 5፥17) በሌላ አነጋገር፥ “አዲስ ሰው ነኝ፥ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ነኝ። የቀድሞው ነገር አልፏል፥ በሕይወቴ ሁሉ ነገር አዲስ ሆኗል። እኔም አዲስ ሆኛለሁ፥ በአዲስ ጅማሬ ላይ እገኛለሁ።” ማለታችን ነው። መጠመቅ ለጌታና ለማዳኑ በሕዝብ ፊት መመስከር ነው። “የጌታን መንገድ እከተላለሁ፥ ወደ ኋላ አልመለስም።” ማለት ነው።

መስጠት አዲስ ክርስቲያኖችን እግዚአብሔር ከሚያስተምራቸው የመጀመሪያ ነገሮች መካከል አንዱ ነው። ለዚህም ጥሩ ምክንያቶች አሉ። ምክንያቱም መስጠታችን እግዚአብሔር ከሚወዳቸው ነገሮች መካከል አንዱ ስለሆነ ነው። የማቴዎስ ማርቆስና ሉቃስ አንድ ስድስተኛ (ከስድሰት እጅ አንዱ) እንዲሁም ጌታ ከተናገራቸው 38 ምሳሌዎች 12ቱ የሚያተኩሩት ገንዘብን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ነው።

መስጠትን መማር እግዚአብሔርን መምሰልን ከመጀመር ጋር ይነጻጸራል። እግዚአብሔርን መምሰልን ከመጀመር ጋር ይነጻጸራል። “እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ ቅዱስ ሁኑ።“(ሌዋውያን 20፥7፣ 1ኛ ጴጥሮስ 1፥13-16) እግዚአብሔርም በባህሪው የሚሰጥ አምላክ ከመሆኑ የተነሳ እኛም መስጠትን የምናውቅ
እንድንሆን ይፈልጋል። “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና።” (ዮሐንስ 3፥16)

# 8

# መስጠት ይለማመዱ

መስጠት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ ነው። በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ስለመስጠት መመሪያዎችን እናገኛለን። ስንሰጥ መልክና ሥርዓት ባለው ሁኔታ ነው። (1ኛ ቆሮንቶስ 16፥1-2) መስጠት የምንችለውን ያህል ነው። (1ኛ ቆሮንቶስ 16፥2) መስዋዕትነት የተከፈለበት ስጦታ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል። (ማርቆስ 12፥43-44) በእግዚአብሔር አነሳሽነት ግብታዊ ሊሆን ይችላል። (የሐዋርያት ሥራ 2፥45) በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ሕይወታችን ይህንን መመሪያ መማር በጣም ጠቃሚ ነው።

መሰጠትን መለማመድ በስጦታ ማመስገንን ወይም ምስጋናን መግለጽን መለማመድ ነው። ልብና እጅ አብረው የሚሄዱ ናቸው። ልባችን በእግዚአብሔር ምስጋና ሲሞላ እጃችን ደግሞ በመስጠት ያንን ምስጋና ይገልጸዋል ።

ከእግዚአብሔር የበለጠ ምስጋናችን የሚገባው ማን አለ? ያፈቅረናል፣ ልጁን ለኛ አሳልፎ ሰጥቶናል፣ አድኖናል። የልጁን መልክ ለመምሰል ዕድገት መጀመራችን ነው። ከነዚህ የዕድገት ደረጃዎች አንዱ መስጠትን መማር ነው። ረዘም ላለ ጊዜ ከጌታ ጋር ሊያሳልፉት ወይም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በመስጠት ሊያሳልፉት ይችላሉ። በየሳምንቱ ከገቢዎ ለይተው ለጌታ የሚሰጥ ያስቀምጡ። ከዚያም በቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ሥራ ይሆን ዘንድ ይስጡ። በተጨማሪም በቻሉት መጠን በአንዳንድ መንገድ ለእምነትዎ የሚረዱ ክርስቲያናዊ አገልግሎቶችንና በጎ አድራጎቶችን በገንዘብ ይደግፉ።

በማንኛውም ጊዜ እግዚአብሔር እንደሰጠዎ ከሰጠዎ ላይ መልሰው የመስጠትን ሕይወት ይማሩ። መስጠት በክርስትና ሕይወት ውስጥ ደስ ከሚያሰኙ ነገሮች አንዱ ሲሆን በክርስትና ሕይወት ከምንማራቸው ቀዳሚ ነገሮች አንዱ ነው።




© 2007 የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተክርስቲያን HOUSTON, TEXAS



የእግዚአብሔርን ቃል በቃል ማጥናት ግዴታ ሳይሆን ልዩ ችሮታ ነው። ጥቅሙ ለኛ ሆኖ ደስታው ግን ለእርሱ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በቃል ማጥናት ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት ነው። መዝሙር 119ን ብቻ ብንመለከት፥

ቁጥር 89 “አቤቱ ቃልህ በሰማይ ለዘላለም ይኖራል።”

ቁጥር 105 “ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው።”

ቁጥር 162 “ብዙ ምርኮ እንዳገኘ በቃልህ ደስ አለኝ።”

ጸሐፊው ለእግዚአብሔር ቃል ይህን ያህል ግምት የሰጠው ለእግዚአብሔር ትልቅ አክብሮት ስላለው ነው። ቃሉ የርሱነቱ ነጸብራቅ ነውና። እግዚአብሔር የልቡን ዘርዝሮ ለኛ ያሳየን በቃሉ ነው።

# 9

# የእግዚአብሔርን ቃል በቃልዎ ያጥኑ

የእግዚአብሔርን ቃል በቃል ማጥናት አንዳንዴ “ቃሉን በልብ መሰወር” ተብሎ ይታወቃል። ይህን ስናደርግ፥ የእግዚአብሔርን ኃይል በልባችን እንደ ደበቅን ይቆጠራል። እግዚአብሔር የጻፈው አንድ መጽሐፍ ብቻ ነው። ያንን መጽሐፍ በልባችን ውስጥ በመደበቅ ለእግዚአብሔር ያለንን ክብር እንገልጽለታለን። “አቤቱ፥ ሕግህን እንደምን እጅግ ወደድሁ! ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው።” (መዝሙር 119፥97)

የእግዚአብሔርን ቃል በቃላችን የምናጠናበት አንዱ ምክንያት ደግሞ ከኃጢአት እንድንጠበቅ ነው። መዝሙረኛው ዳዊት በመዝሙር 119፥11 እንዲህ አለ፥ “አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ። ” ኃጢአት በሚፈታተንዎ ጊዜ ጠንካራ መካላከያ ያስፈልግዎታል። እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ያንን መከላከያ አዘጋጅቶልዎታል። በርከት ያለ የእግዚአብሔር ቃል በቃልዎ ሲይዙ፥ ፈታኙ በሚመጣበት ጊዜ ዝግጁ ሆነው ይጠብቁታል። በኃጢአት ሊጥልዎ በሚመጣበት ጊዜ የሚያዋጣዎ በደህና ጊዜ በልብዎ የሸሸጉት የእግዚአብሔር ቃል ነው።

# 10

# ተጠሪ የሚሆኑለት ፈቃደኛ የሆነ ሰው ያዘጋጁ

> አብሮዎ ይፀልያል፣ ያበረታታዎታል፣ ወደ ጀመሩት አዲስ የሕይወት ጎዳና ተመልሰው ጉዞዎን በቅጡ እንዲገፋበት ያደርጋል።

ለእግዚአብሔር ያለዎ ተጠሪነት/ታዛዥነት እየጨመረ በሄደ ቁጥር፥ በችሎታዎ፣ በፅናትዎና በኃላፊነትዎ እያደገ ይሄዳሉ። ይህንን ለማድረግ አንደኛው መንገድ አብሮዎ በዚህ ሕይወት ውስጥ የሚጓዝ፥ ቃል የገቡትን መፈጸምዎን የሚመለከት፥ ሲደክቡ የሚያበረታታዎ፥ ጸሎት ሲያስፈልገዎ በጸሎት የሚያግዝዎ አንድ ተጠሪ የሚሆኑለት ወዳጅ ማበጀት ነው።

ተጠሪ የሚሆኑለት ወዳጅ ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ሰው በክርስትና ሕይወቱ የበሰለ፣ እርስዎም በክርስትና ሕይወትዎ እንዲበስሉ የተቻለውን ሁሉ ሊያደርግ የሚችል ማለት ነው። ይህ ሰው በአንዳንድ ጉዳዮች ኃላፊነትዎን መወጣትዎን ለማወቅ ሊጠይቅዎ የሚችልና አደርገዋለሁ ያሉትን ነገር ማድረግዎን እርግጠኛ እንዲሆኑ በመርዳት ወደ ግብዎ ሊገፋፋዎ የሚችል ሰው ማለት ነው።

ለምሳሌ ያህል፥ ተጠሪ ሊሆኑለት ለወሰኑት ሰው በየዕለቱ በማለዳ ለግማሽ ሰዓት የጸጥታ ጊዜ ይኖረኛል ካሉ፥ ይህ ተጠሪ የሆኑለት ሰው ወደ ቀኑ ግማሽ ላይ ስልክ በመደወል ስለጸጥታ ጊዜዎ ሁኔታ ሊያነጋግረዎ ይችላል። ለእግዚአብሔር ቃል የገቡትን ሁሉ ማድረግ አለማድረግዎን ይከታተላል።

የተጠሪነት ጉዳይ ብዙውን ጊዜ በሁለት አቅጣጫ ይሄዳል። ተጠሪ ለሁንልዎ ለወሰነው ሰው እርስዎም ለርሱ ተጠሪ ሊሆኑለት ይችላሉ። እንዲዚህ በሚሆንበት ጊዜ አንደኛው ሲደክም ሌላው እየደገፈ በእምነታችሁ በጋራ በመበርታት ለመጓዝ ጠቃሚ ነው።

ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ጥሩ አምሳያ በመጽሐፈ መክብብ ሰፍሮ ይገኛል። "ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻልል። አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሳው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት።" (መክብብ 4፥9-10)

ይህ መመሪያ በአካላዊው ዓለም ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊውም ዓለም ተመሳሳይ ውጤት አለው። ቢወድቁ የሚያነሳዎ ወዳጅ አለዎ ማለት ነው። ከጌታ ጋር ባለዎ ጉዞ የቸልተኛነት ሁኔታ ካሳዩ፥ ይህ ሰው ቀስ ብሎ በመንፈሳዊ ሕይወት ጉዞዎ አደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳሉ በማሳሰብ አካሄድዎን እንዲያስተካክሉ ሊረዳዎ ይችላል።
የድሮ የመካከለኛው ምሥራቅ አባባል አለ፥ "ወዳጅ የሚያስጠነቅቅ ነው።" ጥሩ ወዳጅ ይልቁንም ተጠሪ የሆኑለት ሰው በማስጠንቀቅ ብቻ አያበቃም።

መልካም ወዳጆች ተቺዎች አይደሉም ... ይረዳሉ። ጥሩ ጓደኛ በሚደክሙበት ጊዜ አብሮዎ ሊያዝን አይመጣም። ነገር ግን፥ ኃይልዎን አሰባስበው እንዲበረታቱ ያደርጋል እንጂ። እርስዎና ሌላ ክርስቲያን በእንደዚህ ያለ መተባበር ስትጓዙ በሁለታችሁም ውስጥ ያሉ ምርጥ ነገሮች ይወጣሉ።





# ማጠቃለያ

በቅርቡ መድኃኒትዎ አድረገው ሊቀበሉት ወደ ክርስቶስ ከመጡ፥ የክርስትና ሕይወትዎን በትክክል መጀመርዎ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ነው። አሁን አዲስ ሕይወት አለዎ፥ ማደግ ደግሞ ይጠበቅብዎታል። ማደግ የመወለድን ያህል አስፈላጊ ነው። አንድ ልጅ ተወልዶ እንደ ነበረ ትንሽ ሆኖ ቢቀርና ባያድግ ምንኛ የሚያሳዝን ነገር ነው? እርስዎም በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም ተወልደው ሳያድጉ ቢቀሩ ያንኑ ያህል አሳዛኝ ነው።

እነዚህ አስር ነጥቦች በውስጣቸው ተአምራዊ የሆነ ፎርሙላ የያዙ አይደሉም። ነገር ግን፥ ከእግዚአብሔር ቃል የተውጣጡና በብዙ ትውልዶች የነበሩ የበሰሉ ክርስቲያኖች ያለፉበትን ልምድ መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው። እነዚህን አስር ነጥቦች በሙሉ ልብዎ ቢከተሉ፥ ጉዞዎ በውጣ ውረድ የተሞላ ቢሆንም ደስ የሚያሰኝና የሚባረኩበት ይሆናል።

ለማደግ በሚያደርጉት ጉዞ እግዚአብሔር ይርዳዎ!

© 2007 የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተክርስቲያን HOUSTON, TEXAS